# ኢትዮጵያን የጠበበ ጥብቆ ገዢነትና ፖለቲካ

**ባዩ ደግፌ**

***ታህሳስ 2001***

**1)** ዓለምን የተቆጣጠረው ሊበራል ኢኮኖሚ ግንባታውና ንግሡ በመንግስት ተሳትፎ የተከናወነ ነውና ገና ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መግባት የሚሹ አገሮች መንግስታት የልማት አጋፋሪ መሆን ግዴታቸው ነው:: በኢህአዴግ መንግስት ላይ ያለው አንዱ ሁነኛ ቅሬታ የልማታዊ መንግሰትነት ብልህ ሚናን ባግባቡ እየተወጣህ አይደለም የሚል ነው:: በልማት አሳቦም ይሁን/አይሁን ዲሞክራሲን መሸሽና ማፈን የሚፈልግ ገገር የህዝብ ድምፅንና ጠያቂነትን የሚፈራ ብቻ ነው:: የተቀየሰ የልማት ፖሊስ በየምርጫ ዙር ሊመጣ በሚችል የመንግስት ለውጥ ምክንያት መቀያየር እንደሌለበት እሙን ነው:: ነገር ግን ይህ ሀቅ የአንድ ፓርቲን የማይቋረጥ የበላይነት ተገቢ ለማድረግ ምክንያት አይሆንም:: የመንግስት ልማታዊነትና ያንድ ፓርቲ የበላይነት የተለያዩ ነገሮች ናቸው:: የመንግስት ልማታዊ ሚና ቻይና ውስጥ እንዳለ ሁሉ ህንድም ውስጥ አለ::

በኢንዱስትሪ በለሙ አገሮች የሚታየው የፓርቲዎች አገራዊ የጋራ መግባባት እንደ ኢትዮጵያ ኋላቀር በሆኑ አገሮች ተጫባጭ ሊሆን እንደማይችል አድርጎ መከራከር ስህተት ብቻ ሳይሆን አጭበርባሪነት ነው:: በኢትዮጵያ ሁኔታ ላይ ተወሰነን ብንነጋገር እስካዛሬ ድረስ ከባላጋራነት ተወጥቶ እውነተኛ የመቀራረብና የመደራደር ጥረት ሲሞከርና ሲከሽፍ አልታየም:: የራስን አላማ አማራጭ የለሽ ወይም ስለሁሉ አድርጎ ከማስተጋባትና ለፕሮፓጋንዳ ጠቀሜታ ያክል የሚሆን ውይይት ከማድረግ አልታለፈም:: ህወሃት ኢህአዴግ የራሱን በስልጣን መቆየት ግዴታ አድርጎ ወስዶታልና በማንኛውም መንገድ ስልጣኑን ማስቀጠልና በ«ጸር»ነት የሚያያቸውን ቡድኖች ማጥቃት አስቀድሞ የደመደመው ጉዳይ ነው:: በዚህም ምክንያት ሰፊ የህዝብ ድጋፍ ያለው መንግስታዊ አመራር እንዳይደራጅ አግዷል:: ለአገር ልማት አብረን እንስራ÷ በጠላትነት መተያየት ቀርቶ የእርቅ አመለካከት ይፈጠር ሲባል (መስማሚያ ቀርያ የሚቀስቅስ ተቃዋሚ ባይታይም) «እርቅ ስልጣንን በአቋራጭ ለመያዝ የሚደረግ ጥገኝት ነው» ባይ ነው:: በምርጫ ውድድር ሲመጡበትም ነፃ እድል ሊሰጥ አይደፍርም:: ይኸ ቀርቶ ከአዲስ አበባ ወጣ ብለው ቢሮ ለመክፈትና ለመቀስቀስ እንዳይችሉ በስውር ማስፈራሪያ የሚቀርባቸው ሰው እንዳይኖር ያደርጋል:: የውስጥ የፖለቲካ መረጋጋት እንዳይፈጠር እንቅፋት ሆኖ÷ የህዝብ ድጋፍ ድሃ ሆኖና ነፃ ምርጫን ፈርቶ ለልማት ግን አስፈለጊ ነኝ ይላል:: ተቃዋሚዎቹንም ይፀየፋል::

የሚፀየፋቸው አቢዮታዊ ዲሞክራት ስላልሆኑ ይሆን? ለመሆኑ ለብዙ ሰው አልጨበጥ ያለው አቢዮታዊ ዲሞክራሲ ምንድን ነው? ህወሐት/ኢህአዴግ ዛሬም ከግራ ፖለቲካና አላማ አልወጣም ብሎ ማሰብ ወይም ለህዝብ የምዋደቅ አቢዮታዊ ነኝ ባይነቱን ባህርይው አድርጎ መውሰድ እውነቱን ለመረዳት አያስችለንም:: ግራነት ኖረበትም አልኖረበትም አሁን በኢትዮጵያ «እየገነባ» ያለው የከበርቴ ስርአተ-ኢኮኖሚ ነው:: ተቃዋሚዎቹ ከዚህ የተለየ ይሁን አላሉም:: ህወሐት/ኢህአዴግ ከመደቦችና ከጥቅም በላይ ሆኖ መንግስትን የሚመራ ኃይል አይደለም:: በቢሮክራት ከበርቴነትም ይሁን በግልፅና በእጅአዙር ግላዊ ባህብትነት የላይ መደብ ሽግግሩን እያቀላጠፈ ነው:: በወረቀት ላይ ከበርቴው በጥገኝነት ልማቱን ሊጎዳ የሚችል ተግባር ስለሚፈፅም ልማታዊ ካልሆነ በቀር አጋር አይደለም እየተባለ ቢጻፍም÷ የሞቀ ትርፍ በታየበት አካባቢ ገገሮቻችን የተከለለ ሽርክና እያበጁ ከጠበሉ ሲካፈሉ እያየን ነው:: እንደሾላ

የተንተረከከው የሰንሻይን ኮንስትራክሽን ዋና ባለሀብት ባደባባይ ባለቤት የሚባለው ግለሰብ እንዳልሆነ ይታወቃል። የጥገኝነትና የሙስና ፀር ነኝ ባይነቱ ጆሮ ቢያስለችም የኢትዮጵያን ሕዝብ ሀብት እየመነዘሩ አጋርና ደጋፊ የመግዛቱ ተግባር ካገር ውስጥ አልፎ ባህርማዶም ተሻግሯል። መንግስታዊ ገንዘብ በተለያየ ስልት ወደ ግል ኪስ ይታለባል። በመንግስታዊ ሹሞችና በአጋጣሚ አባራሪዎች ቅንብር የመንገድ ዳር ክፍት ቦታ ባልታወቀ ሁኔታ ተይዞ ፈጣን ትርፍ አምጪ ንግዶች ይለቀቁበታል። ለንግድ አይን የሆነ የከተማ ቦታን በሊዝ ተመርቶና ዙሪያውን ንግድ ቤቶች ገጥግጦ በማከራየት ላይ ብድር ተጨምሮበት ከባዶ ኪስ ባለህንፃና ኢንቬስተር ይወለዳል። ከተቀነባበረ የቀረጥ ማቅለልና ሽወዳ ባሻገር ለአቢዮታዊ ዲሞክራሲ ቅርብ የሆኑ አስመጪዎችና ተጫራቾች በብቸኛና በዋነኛ አቅራቢነት ገበያውን የማጥለቅለቅ እድሎች አግኝተው ባንድ ጀንበር ሰማይ መውጣት ችለዋል። የህወሐት/ኢህአዴግ ገዢዎች ስልጣኑ የኛ ብቻ ይሁን ብለው ድርቅ ያሉት የሚያኮሩ ንፅህና ኖሯቸው ወይ የ«ልማታዊነት» ባህርያቸው ተኪ የለሽ ሆኖ አይደለም። እውነተኛው ምክንያት **ለዚህ ስልጣን ከኛ በላይ የተዋደቀና የደማ የለም** ነው። የአቢዮታዊ ዲሞክራሲም **እምብርት ይዘት** ይህ ነው። «የብሔሮች መብትና ህገመንግስት እንዳይቀለበስ» እና «ሰው በላው ስርአት እንዳይመለስ» መታገል፥ ልማታዊ መንግስት ነኝ፥ ባንድ ፓርቲ «ዲሞክራሲ» ካልሆነ በተቀር ከፓርቲዎች ጋር ሀገራዊ መግባባት ፈጥሮ የገዢነት መፈራረቅ ባለበት ሁኔታ ልማትን ቀጣይ ማድረግ አይቻልም ባይነታቸው ሁሉ -- ማለትም የ«አብዮታዊ ዲሞክራሲ» ፖለቲካቸው -- የድል ፍሬ ተደርጋ የምትታየውን ስልጣንን ማስከበሪያ መሳሪያዎች ናቸው።

**2)** በመለስ ዜናዊ የሚመራው የህወሀት/ኢህአዴግ ገዢነት የሁሉ ነገር እምብርት ነው። የልማት መርሐግብሩ ስልጣን በማስጠበቅ ቀመር ላይ የተበጀ ነው። በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ መፅሐፍ ገፅ 61 ላይ ሳይደበቅ እንደተቀመጠው 85% ከመቶ የሆነውን አርሶ አደሩን በአጋርነት መያዝ ስልጣንን የማስጠበቅ ዋስትና ነው። የግብርና መር ልማት የዚሁ ማስፈፀሚያ ነው። የትም መቼም ተቃዋሚን እንደፀር አድርጎ ማየትና እንዲታይ ማድረግ፥ ከህዝብ ጋር እንዳይደራረስ አደርጎ ማንሳፈፍ፥ አማራጭ የለሽ ምርጫ ማካሄድ፥ አማራጭ ብጤ ቢኖር እንኳ በጫናና በሻጥር የምርጫ ውጤትን መቆጣጠር፥ ከዚህ ካለፈ ወታደራዊ ጉልበት መጠቀምና ተቃዋሚን የደገፉ ሰዎችንና ለተቃማዊ ያደላ የምርጫ ውጤት ያላቸውን ጣቢያዎች አመሳቅሎ በማሸት ለመጪው ጊዜ መግራት የአቢዮታዊ ዲሞክራሲ ስልቶቹ ናቸው።

ከቅርብ ጊዜ በፊት ኢሕአዴጎች በ«ታነጹበት» <u>አገራዊ ለውጦች፣ ቀጣይ ፈተናዎችና አቢዮታው ዲሞክራሲያዊ መፍትሄዎች</u>[1] የተሰኘ ሰነድ ውስጥ ለሚወራለት ልማትም የመአዘን ድንጋይ ሆኖ የምናገኘው የህወሃት/ኢህአዴግ ስልጣን ቀጣይነት ነው። ይህ መፅሐፍ አንድ ብሎ የሚጀምረው «የቅድመ ተሃድሶው መስመር የግብርና ልማትን በምግብ ራስን በመቻል ማፅቀፍ የሚያየውና ይኸው ሂደት በገጠር ሰፋ ያለ የመደብ መራራቅ እንዳይፈጠር በማገድ ላይ ያተኮረ ስትራተጅ የነበረ» መሆኑን በመግለፅ ነው።(2) የህወሃት ኢህአዴግ የድርጅትና የፖለቲካ አትኩሮትም «በድሃወና ባጣ በነጣው አርሶአደር ላይ» ነበር። (5) የሀብት መራራቅ እንዳይፈጠር

[1] ከዚህ በኋላ የገጽ ቁጥር ብቻ በማስቀመጥ የሚጠቀሰው ይህ መጽሐፍ ይሆናል።

እድገትን ሰንክሎ ከደሃው አርሶአደር ጋር የመጣበቁ ግብ የብዙሃኑን የፖለቲካ ድጋፍ ማግኘት ነበር፡፡ ነገር ግን የረባ የልማት ፍሬ ሊያሳይ (የብዙሃኑ አርሶ አደር አለኝታ ለመሆን የሚያበቃ ኑሮና መልካም አስተዳደር ሊያመጣ) አልቻለምና ምርጫ ከማጭበርበር አልወጣም ነበር፡፡

ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትና ከህወሓት ድርጅታዊ ቀውስ መልስ በ«ተሃድሶ» ስትራቴጂው ላይ ማስተካከያ አደረገና ሀብታም አርሶ አደርን የመፍጠር ንድፍ አወጣ፡፡ የስትራቴጂ መፅሐፎች እያተሙ መበተንና በነዚያ ላይ ማወያየት፥ የግብርና ልማት ሰራተኛ ስልጠና፥ የገበሬ ማስልጠኛ ምስረታና የገቢ እድገት የሚያስገኙ የግብርና ልማቶች የማካሄድ ሩጫ ቢጀማመርም ለ1997 ምርጫ የሚደርስ የለውጥ ውጤት አልተገኘም ነበር፡፡ በቀድሞዎቹ ጊዜያት ያልታየ የህዝብ እውነተኛ ስሜት ያረፈበት ብርቅ ምርጫ ቢካሄድ፥ «የከተማውንና የከበርቴውን የፖለቲካና የገንዘብ ድጋፍ ሳንፈልግ በአርሶአደር ድጋፍ ያለሀሳብ እንገዛለን» የሚለው የህወሓት/ኢህአዴግ ቀመር ሬሳው ወጣ፡፡

በኃይልና በፕሮፓጋንዳ ድቆሳ ስልጣኑን ከስጋት ካወጣ በኋላ ዳተኛ የገጠር ልማቱ በአርሶ አደሩ ገቢ ላይ የጭማሪ አረፋ ፈጥሮ የፖለቲካ ድጋፍን እንዲወልድ በነበሩና አዲስ ባደረጃቸው (ፖለቲካዊ አመራር በሚሰጣቸው) የገበሬ ህብረት ስራ ማህበራትና ዩኒየኖች አማካይነት እንዲሁም በመንግስታዊ ግዢው ወደገበያ የሚገባውን የግብርና ምርት ብዛት ሸምቅቆ ዋጋ የመስቀል መድሃኒት ተጠቀመና የቀናቸውን ገበሬዎች ገቢ አነሳ፡፡ ይህ ክንዋኔ «አርሶ አደሩ በዋጋ ውድቀት ልፋቱን እንዳይዘረፍ እየተባለ በግልጽ የተቀናበረ ነው፡፡ ከእግዲህም የዋጋ ውድቀት ስጋት እንዳይኖር መቆጣጠሪያው ተበጅቷል፡፡ ነጋዴው የደረሰበትን የትርፍ መቀነስ በሸማቹ ላይ አሸጋግሮ ሲያስመልስና የከተሜውን ደሃ ወደ ከፊል ረሃብ የከተተ ጉዳት ሲደርስ ምርት የደበቁ እንዲያወጡና ዋጋ እንዲረጋጋ ግፊት የመስጠት የመንግስት ሽርጉዶችም ያንገት በላይ ማደናገሪያዎች ነበሩ፡፡ ነጋዴውን  እህል አከማቻህ እያለ ሲረብሽና ሲቀጣ ዩኒየኖችን አለመንካቱን ያስተውሷል፡፡

ከለምነትና ከሌሎች አመቺ ሁኔታዎች ጋር የግብርና ልማቱና ዋጋ ሰቀላው ተገናኝቶ ሊነሱ የቻሉና የከፊል ነጋዴነት ባህርይ ያላቸው ጥቂት ሀብታም አርሶአደሮች ስኬት በሬዲዮና በቴሌቪዥን እየተወሳ የገበያ-መር ግብርና ልማቱ ተሞገሰ፡፡ የልማት ጀግኖች እየተመረጡ ተሸለሙ ፡፡ የኢህአደጌ <u>አገራዊ ለውጦች ...</u>  መጽሐፍ እንዳለው በኢትዮጵያ የዋጋ መውደቅ መቀስ ግብርናን አልቆረጠውምና «የገጠር ብር ከተማ መከማቸቱ ቀርቶ የከተማ ብር ገጠር የሚከማችበት ሁኔታ» ሊፈጠር ቻለ፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው «በአለም ገበያ በታየው ለውጥና መሰል ምክንያቶች» ነው ብሎ ማለት (11-12) ግን አይን ያወጣ ቅጥፈት ነው፡፡

ባጠቃላይ ከልማቱና ከዋጋ ሰቀላው እንዲሁም ከየግል ተጓዳኝ ጥረቶች ሊያተርፍ በቻለውና በዚያ ሂደት ውስጥ በሚገኘው የአርሶአደር ክፍል ላይ ኢህአዴግ መልህቁን ጥሏል፥ የልማቴ ውጤት እያለ፡፡ ወደፊት አታካች የእገዛ ጥረት ሳይጠይቁ ከየቦታው ልቀው የሚወጡትን የገጠር ሀብታሞችና ሀብታም ብጤዎች በዙሪያው ማሰባሰቡን ይቀጥላል፡፡ ሀብት ማካበት የቻሉት ግብርናቸውን ከማስፋት ሌላ በወፍጮ አገልግሎት፥ በሸቀጥ ንግዱና በመሳሰሉት የኑሮ መስኮች እየተሰረጫጩ  የገጠሩን የኢኮኖሚ ህይወት  እንደሚመሩት ሁሉ ባስተሳሰብም ጭራቸው ማድረግ እንደሚችሉ ገብቶታል፡፡ አመጣጣቸው አነሰም በዛ ከኢህአዴግ

የልማት ፕሮግራም ጋር ተያያዥ እንደመሆኑ ገዢነቱን ይደግፋሉ፥ ልማቱ ሊያሳድጋቸው እስከቻለ ድረስም ድጋፋቸው ይቀጥላል፥ በፖለቲካ ግርግር የኢኮኖሚ ግስጋሴያቸው እንዳይደናቀፍ ስለሚፈልጉም ተቃዋሚዎችን/«የሰላም ፀሮችን» በቁርጠኝነት ይታገሉልኛል፥ ስለዚህ እነሱን መያዝ መላውን ገጠር መቆጣጠር ነው፤ የኢህአዴግ ያልተደበቀ ስሌት ይህ ነው:: በዚህ ስሌት መሰረትም አዲሱን ሀብታም በኢቢዮታዊ ዲሞክራሲ እያጠመቀ የገጠሩን የኢህአዴግና የመንግስት አመራር እንዲቆጣጠሩ አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል:: ወደፊትም ከልማት ተግባራቸው ሳይፈናቀሉ የትምህርት ቤቶችንና የጤና ተቋማትን፥ የሴትና የወጣት ማህበራትን አመራር፥ የወረዳ ምክር ቤቶችንም እንዲቆጣጠሩ አስቧል (33-54):: በኢህአዴግ አነጋገር ሀብታም አርሶ አደር «የገጠሩን ህዝብ በዙሪያው ለማሽከርከር ብቃቱ ያለው ሃይል ነው::» «የገጠርን ገንዘብና ምርት አፍኖ በመያዝ ብቻ ማንኛውንም ሃይል፣ ኢህአዴግንም ... ሊያንበረክክ የሚችል ሃይል ነው:: ... »(30) «ኢህአዴግ ከእንግዲህ ከዚህ ሃይል መሰረታዊ ጥቅሞች ውጪ መሄድ አይችልም፤...» (31)

ሆኖም የህወሐት/ኢህአዴግ ገዢነት «በገጠር ሳምባ የሚተነፍስ» ሆኖ ቢወሰን ሊዘልቅ አይችልምና «በተለያዩ ንፋሶች በቀላሉ የሚናጋ ሆኖ» የሚገኘው የከተማው አቢዮታዊ ዲሞክራሲ «የራሱ ደልዳላ መሰረት» እንዲያገኝ በገጠሩ አይነት ስትራቴጂ ተቀይሶለታል:: «የከተማውን ህዝብ በወሳኝ መልኩ የሚያስተዳድር የከተማ ሀብትም» መፍጠር (37):: ከተማ ውስጥ ሀብታም ጠፍቶ አይደለም:: ኢህአዴግ የሚያወራው ስለነባሩ ሀብታም ሳይሆን ከጥቃቅንና ከአነስተኛ ተቋማች ልማት መርሐ ግብሩ አብራክ ተወልዶ ለባለውለታው ለኢህአዴግ ስልጣን ጠንካራ መሳሪያ ሊሆን ስለሚችል አዲስ ሃብታም ነው:: «በከተማ ከሀብታም አርሶ አደሩ የሚመሳሰል ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሃይል እንደምንም ተረባርቦ መፍጠርና ፈጥኖ የአመራር ቦታውን እንዲይዝ ማድረግ **ከሁሉም ነገር በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ** ጉዳይ ነው::» ይላል ኢህአዴግ:: (ቅልመት የተጨመረ፥ 54)

**3)** መለስና ጭፍሮቹ ለስልጣናችን ይጠቅመናል ያሉት ክፍል ላይ መጣበቃቸው የራሳቸው ጉዳይ ነው:: ለነሱ የስልጣን ንድፍ የሀገሪቱ ልማት መገበር ግን አይኖርበትም:: የህወሐት ኢህአዴግ ገዢዎች ረዥም የስልጣን እድሜ - ግብ፥ ግብርና መር ልማት ደግሞ የዚህ ግብ መሳኪያ መሳሪያ መሆኑ ተገልብጦ፤ ግብርናና ኢንዱስትሪ የተሳሰሩበት የኢኮኖሚ፥ የፍትህና የዲሞክራሲ ግንባታ - ግብ፥ የፓርቲዎች ፖሊተካዊ ሚናና ስልጣን ደግሞ የግቡ መሳሪያ እንዲሆን ነው ሀገሪቱ የምትፈልገው::

የሀገር ልማት ስኬቱ የሚለካው ከገጠርና ከከተማ ሊፈጠር በሚችለው ሀብታም ልክ ሳይሆን የብዙሃኑን ድህነት በማቃለል ስፋቱ ነው:: አንድ ቦታ ላይ ያለን ቀዳዳ ለመጣፍ ሌላ ቦታ ላይ ቀዳዳ መፍጠር ልማት አይደለም:: የውስጥ ፍጆታ ምርቶችን ልማት መጉዳትና ከአገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ በውጪ ገበያ የመዝለቅ እድል ያለውን የጤፍ ሰብልን ምህዳር በአበባ እርሻ ማጥቃት ማልማት ሳይሆን ማጥፋት ነው:: የእቃ እጥረቱ ሳያንስ ገበያ ውስጥ መአት ብር እየረጩ ዋጋ ንረትን ማንደርደር፥ ዜጎች ሌባ ከሚሰርቀን በሚል ባንክ ከሚያስቀምጧትና ግሽበት ከሚያራግፋት ቁጠባ ላይ ግብር ማቃፈፍ፥ ሆድን ማሸነፍ በከበደበት ኑሮ ላይ

የኤለክትሪክ መብራት መቋረጥን ችግር አክሎ እጥፍ በጥፍ ለተወደደ የሻማና የፋኖስ ወጪ ህዝብን መዳረግ ድህንነትን ማገዝ ነው:: የመንግስት ቤት አከራይነት ላይ ሙዝዝ ብሎ የተከራይ አከራይ ሆናችኋል፥ ንግድ ከፍታችኋል ወይም ተጨማሪ ቤት ገንብታችኋል እያሉ ተከራይን ማተራመስ «ኪራይ ሰብሳቢነትን» መታገልም ለፍትህ መቆምም ሳይሆን የቤት ችግርን ማባባስ ነው::

ልማቱ ደንበር-ገትር ከማለት ወጥቶ ባጠቃላይ የገጠሩንና የከተሜውን የኑሮ ክብደት የማቅለል እርምጃ ውስጥ መግባት ይፈለግበታል:: ጤናማ ግስጋሴ ተፈጥሮን ከማበልጸግና ከመንከባከብ ጋር ምርታማነትን የሚያሳድጉ ቴክኖሎጂዎችን በሰፊው ማስረጽና ድንገተኛ ያየር መዛባትን መቋቋም የሚያስችል ቅርስ የመፍጠር ትልምን ይፈልጋል:: ዋጋን ከፍና ዝቅ ከማስድረግ ጨዋታ ወጥቶ የማዳበሪያና የምርጥ ዘር ውድነት በገቢ አድራቂነት የሚያሳድረውን ተጽእና የሚቀይር ለውጥ ማምጣት፥ እንዲሁም ቀልጣፋና አማራጨ-ብዙ የገበያ ስርአት በማዳበር በገበሬውና በሸማቹ ላይ የሚደርሰውን ገፈፋ ማቃለል ይጠይቃል:: ጥቃቅንና አነስተኛ ስራዎችን የማስፋፋቱ እንቅስቃሴ በተለመዱት የሽቀጥ ችርቻሮ፥ የሽመና፥ የእንጨት፥ የብረታብረት፥ የጸጉር ወዘተ ስራዎች ውስጥ ከመሽከርከር ውሱንነት ወጥቶ ከእንዱስትሪና ከግብርና ልማት ጋር የተቀናበረ ስፋት ማግኘት ይገባዋል:: ለወጪ ንግድ ደንበኝነት ተብሎም ይሁን በንዝህላልነት፥ የአገር ዜጎች በጥራት-የለሽና በሀሰተኛ ገቢ-ምርቶችና መድሃኒቶች መጠቃት አይኖርባቸውም:: የአገር ውስጥ ገበያን ከነዚህ ምርቶች መጠበቅና በጥራት የማምረት ውስጣዊ አቅምን በማዳበር ችግሩን መፍታት ግድ ነው:: ከመንግስት እስከ ግለሰብ ድረስ በተንሰራፋብን የውጪ ዕቃ አምላኪነትና አግበስባሽነት ላይ የባህል ለውጥ እስካልተደረገም እየከነፈ ያለውን የንግድ ጉደለት መቆጣጠር አይቻልም:: ለበለፀጉ አገሮች የግብርና ውጤቶችን በብቃት ለማቅረብ ከመልፋት ባሻገር፥ የጥራት ችግር በሌለባቸው ኢንድስትሪያዊ የፍጆታ ቁሳቁሶችም በኩል ያሉትን የገበያ ዕድሎች ባግባቡ ለመጠቀምና ስም ለማግኘት መፍጠን ወሳኝ ነው:: በበለፀጉት አገሮች ገበያ ላይ እንዲንጠለጠል የተደረገ ኢኮኖሚ እነሱ ደንበኛ ሲቀይሩ፥ ሲያኮርፉ፥ ወይም ቀውስ በመታቸው ቁጥር የሚሽመደመድ ነውና ከጎረቤቶችና ከብጤዎች ጋር የገበያና የልማት ትስስርም ትኩረት ማግኘት ይኖርበታል:: ልማታችን እነዚህን ሁሉ አቅጣጫዎች ያካተተ ትልም ይፈልጋል::

መች ተነካና ሊባል የሚችለው የአገሪቱ ምንጨ-ብዙ እምቅ የኤሌትሪክ ሀብት[2] ለሀገሪቱ ኢንዱስትሪያዊ ልማት ከጎረቤት አገሮች ጋር በጋራ ልማት ለመተሳሰር፥ የህዝቡን እለታዊ የሃይል ምንጭ ፍጆታ ፍላጎት በቀላል ዋጋ ለመሙላት፥ የውጪ ነዳጅ ጥገኝነትን ለመቀነስ፥ የእንጨት ማገዶ ተጠቃሚነት በአካባቢ ላይ የሚያደርሰውን መራቆት ለመስቀረት፥ በኤሌክትሪክ ባቡር አገልግሎት የመጓጓዣ እጥረትንና ውድነትን ለማቃለል የሚኖረው ወሳኝ ፋይዳ ከወዲሁ ከሞላጎደል መጤኑ እሰየው ነው:: ግን በዚህ እምቅ ሀብት ታሪክ ለመስራት ከእስካሁን የበለጠ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያሻል:: ባጠቃላይም በሁሉም የልማት አቅጣጫዎች ባገር ውስጥ

---

[2] እንደ ኢህአዴግ አባባል፥ገና ያልተጠናቀቁትን ግንባታዎች ጨምሮ እስካሁን ከውሃ ሃይል ማመንጨት የተቻለው 2ሺ ሜጋዋት ሲሆን፥ ከውሃ ከንፋስና ከእንፋሎት ሊመረት የሚችለው እምቅ የኤሌትሪክ ሃይል ግን ከ60 ሺህ ሜጋዋት ይልቃል:: (አገራዊ ለውጦች ...126-127)

ያለ የግልና የመንግስት አቅምን ከውጪ ከሚገኘው ጋር እያስተባበሩ በብቃት ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል:: አሁን ያለው የመንግስት ፖለቲካና የልማት አመራር ግን ለዚህ ተልእኮ አይመጥንም:: የመንገድ ግንባታዎችን ሳይቀር በውጪ በተለይ በቻይና ኩባንያዎች ማሰራታችን፥ ቻይኖቹ ንቀውን ጥራትን ማልከስከስ ቢጀምሩም የራሳችንን ሙያተኞች ቀጥረው በቅልጥፍና ማሰራት ሲችሉ የኛ የመንግስትና የግል መንገድ ገንቢዎች ግን (ሜድሮክን ጨምሮ) የብኩንነትና የስርቆት መፈንጫ መሆናቸውና አልጠናቀቅ እያሉ «እድሜ ይፍታህ» የሚል ቅፅል ስም እስከማትረፍ መድረሳቸው፥ በሌላ በኩል ባለገንዘቦች የከተማ መሬትና የቤት ግዢን ከግሽበት ኪሳራ ገንዘብን አድኖ ለማስቀመጥ እየተገለገሉበት መሆኑ የውስጥ አቅምን በማሰራት በኩል ያለብንን ችግር ያመለክታሉ::

በልማታችን ፍላጎቶች ላይ የተመሰረቱ ምርምሮችና ፍልስፋዎች እንዲካሄዱ ማመቻቸት፥ የውስጥና የውጪ የቴክኖሎጂና የምርምር መረጃዎችን በተደራጀ መልክ እያሰባሰቡ ለኛ የሚሰማሙትን የመምረጥ፥ የማሻሻልና አእየፈተሹ የማስረፅ አቅምና ስርአት መገንባት ለልማት ወሳኝ መሆኑ አንድና ሁለት የለውም:: ከዚህ አኳያ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ በሚንስቴር ደረጃ መደራጀት የሚደገፍ ነው:: ዩንቨርስቲዎችን የልማት ተዋንያን የማድረግ ጉዳይም ተብሎ ያለቀ ነው:: ችግሩ ግን ዛሬ ያሉት ዩንቨርሲቲዎች እንኳን የምርምርና የፍልስፋ መፍለቂያዎች የመሆን ሚና ሊጫወቱ ይቅርና በየፈረጁ ብቃት ያለው ሙያተኛ እንኳ ማፍራት በማይችሉበት ዝቅጠት ውስጥ የሚገኙ ናቸው:: ዝቅጠቱ የነሱ ብቻ ሳይሆን ከታች ካንደኛ ደረጃ ትምህርት ጀምሮ የተያያዘ ነው:: አያሌ ትምህርት ቤቶች፥ ኮሌጆችና ዩንቨርሲቲዎች ቢኀጋጉም ለየእርከኑ የሚመጥን እውቀትና ስልጠና የሌላቸው ተማሪዎችና በቁጥርም በጥራትም የተጓደሉ መምህራን በግብር ይውጣ ስራ፥ በስርቆት፥ በሽቀጥ አይነት ግብይትና[3] በጅምላ ግፊ አብረው የሚያዘግሙበት፤ ተመርቀውም የህግ ተርጓሚ፥ የስራ ባለሙያ፥ ሊቅና መምህር እየሆኑ ብቃት-የለሽነቱ ኡደት በኡደት የሚጨምርበት እውነታ ነው ያለው::

ይህን የቁልቁለት ጉዞ አቅጣጫ ቀይሮ ወደፊት የመራመድ ጥያቄ በትምህርት ተቋማት ያለውን የተማሪና የአስተማሪ የብቃት ችግር ብቻ ሳይሆን በስራ ገበታዎች ላይ የተበራከተውን ብቃትየለሽነት ጭምር በሆነ ልዩ የማካካሻ መንገድ ማቃናት፥ አብሮም ከተሰደዱ ኢትዮጵያውያንና ከውጪ ቅጥር ሊገኝ የሚችለውን ብቁ ሙያተኛ ጨምሮ በማቀናበር ጥራቱ የተሟላ ትምህርትና ስልጠና ለማካሄድ በሚያበቃ አቅም ብቻ ተወስኖ (ለጊዜው በቁሳቁስና በሙያተኛ መታጠፍ ያለበትን ለይቶና አመት ከተጋመሰ በኋላ ተማሪ እያስገቡ ማሯሯጥን አስቀርቶ) የመስራት ቁርጠኝነት የማይመለጥ ተግባር ሆኖ አፍጧል:: ህወሃት/ኢህአዴግ ግን ለአስራ ምናንም አመታት ያደረሰውን ብልሽት አጢኖ ማፈር ሲገባው ጥራትና ትምህርት ተነጣጥለው በየተራ ይመጡ ይመስል እስካሁን ከ1ኛ ደረጃ እስከ ዩንቨርሲቲ ትምህርትን በሰፊው የማስፋፋት የተሳካ ስራ ስንሰራ ቆይተናል አሁን ደግሞ በጥራቱ ላይ በዋናነት ተግተን እንሰራለን እያለ ይደሰኩራል:: አያሌ ተማሪዎች የተፈጥሮ ሳይንስን የትምህርት መስክ እንዲሸሹ

---

[3] የመመረቂያ ወረቀት ሳይቀር በ«አስጠኚ» አማካይነት ማሰራት ወይምመግዛት የተስፋፋበት ሁኔታ ነው የሚታየው::

ያደረጋቸው በኢትዮጵያ ያለው ፋይዳቢስ የወሬ «ትምህርት» አሰጣጥ ሆኖ ሳለ፥ የተፈጥሮ ሳይንስን ትምህርት «ክብደት»ና ሽሽት የመቀየርም ጉዳይ ከታች ጀምሮ የትምህርቱን አሰጣጥ ከምልከታና ከማድረግ ጋር አስተሳስሮ መገንባትና በዚያው ልክ የስምሪት ምጣኔውን እያሰፋ መምጣትን የሚጠይቅ ሆኖ ሳለ፥ ኢህአዴግ ግን የ2ኛደረጃ ተማሪዎችን የተፈጥሮና የማህበራዊ ሳይንስ ድልድል ወደ 70% እና 30% ምጣኔ የማምጣትን ጉዳይ ቁጥር እንደመቀየር አቅልሎ ወስዶታል:: በመማሪያ መሳሪያዎች፥ በመጻሕፍትና በብቁ መምህራን የተቸገሩ 21 ዩንቨርሲቲዎችን ማቀፋችን አልበቃ ብሎ ሌላ 10 ዩንቨርሲቲዎችን ላልደረሳቸውና «ላነሳቸው» አካባቢዎች ሊያድል ሽርጉድ ይዟል:: የዩንቨርሲዎችን ገዳምነት ለመቀየር አለኝ ያለው መፍትሄም ወጣት «ምሁራንን» በአካዳሚ ውጤት ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ አስተሳሰብ መልምሎ በዚህ 5 አመት ውስጥ «ከተመረጡ የውጭ ዩንቨርስቲዎች (በተለይ የህንድ) ጋር በመታባበር» (የመጀመሪያው አመት በርቀት ትምህርት የሚከናወን) ስልጠናን በማካሄድ በማስተርስ 10ሺ፥ በዶክትሬት 2ሺ ያህል አስመርቆ ማውጣት ነው::(87)

**4)** ለልማቱ የሚዋደቁና የሚመራመሩ ምሁራንን ለማፍራት የፖለቲካ ደጋፊን መመልመል፥ በተማሪነት ወይም ከዚያ በኋላ በድርጅት የታቀፉ ምሩቃንን እየመረጡ ለመንግስት ስራ መቅጠር፥ ከነባር ሰራተኞችም ወደ«አቢዮታዊ ዲሞክራሲ» ሊሳቡ የቻሉትን የስነምግባርና የፖለቲካ ስልጠና እየሰጡ ማስተካከል፥ የማይበገረውን «ባመለካከት/በብቃት ጉደለት» እየገመገሙ ወደ ውጪ መትፋት:: ህወሃት/ኢህአዴግ ትምህርትን ጥራት በጥራት፥ ልማቱን ድጋፍ በድጋፍ ሊያደርግና የስራ ልሽቀትን ሊያጠፋ የተነሳው በዚህ መንገድ ነው::

የተንሰራፋው የጎሪጥ መተያየት፥ የስራ ስሜት ማጣትና አልማጭነት ሁሉ ይበልጡን ከፖለቲካ ቅሬታ ጋር የተያያዘና የዚሁ መግለጫ በሆነበት፤ የኢህአዴግን ፖለቲካ ማዳመቅም የስራ ማግኛና ጥቅም ማባረሪያ የንግድ ፍቃድ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ ፖለቲካዊ መመዘኛንና ፖለቲካዊ ጥምቀትን መፍትሄ አድርጎ መጠቀም እንዴት ውጤት ሊያስገኝ ይችላል? ሰዎች የኢህአዴግ አባልና ደጋፊ የሚሆኑት ባብዛኛው ጥቅም ፍለጋ እንደሆነ ገዢዎቻችን ያቁታል፤ በአደባባይም ተናግረውታል:: አሰልጥነው ያሰማሩት የግብርና ልማት ካድሬ ወደ ሌላ ስራና ሙያ ራሱን እስኪያሽጋግር ድረስ ቀን መግፊያ ሲያደርጋቸው አይተዋል፤ እያዩም ነው:: ስራየለሽ ወጣቶች (የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና ተመራቂዎች ጭምር) ስራ ባገኝ እያሉና ከጀርባ እያፌዙባቸው የኢህአዴግ አባልነትንና ካድሬነቱን ተያይዘዋል:: <u>በአገራዊ ለውጦች...</u> መፅሐፍ ላይ እንደተባለውም «ለኪራይ ሰብሳቢነት ክፉኛ በተጋለጠ ምሁር» መጠቀም ለኢህአዴግ መንግስት አማራጭ የለሽ ሆኖ ቆይቷል (42):: እየሰረቀም ሊያገለግል ይችላል የተባለ እበላ-ባይ ሁሉ ሲያሰማራና አገልግሎቱ ባረጀ ጊዜ ሌላ ሲተካ ነው የኖረው:: እስካሁን ድረስ ስራንና ሰራተኛን የማቃኛ መደበኛ የስራ ስልት አካል ያልሆነውና ስራ ላሽቆ ካበቀለት በኋላ በዘመቻ ሶስቴ (በ1980ዎች ሁለተኛ አጋማሽ፥ በ1994-95፥ አሁንም በ2000-1) የየተካሄደው የ«ግምገማ» ትርምስ የዚሁ አሰራሩ መገለጫ ነው:: የሀብታም አርሶ አደር ስትራቴጂ እየተሳካ ሰለመጣ የተማረው ሃይል ኢህአዴግን በስፋት እየተቀላቀለ ነው፥ «አቢዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ምሁሩ በማያቋረጥ መንገድ የሚቀዳበት የጠራ ሰፊ ሃይቅ ይፈጠርና ... ብቃት ያለው አመራር» ይኖራል

(42-43) የሚባለው ሁሉ የሚታለል ባገኝ ተብሎ የሚነገር ውሸት ነው:: አዲስ «ሃይቅ» የሚባለው በፖለተካ እጥበትና በፓርቲ መዋቅር ሰደድ የሚሊዮኖችን ንቁ ተሳታፊነት እንፈጥራን የሚል እቅድ ነው:: የኢህአዴግ ትልቅ የስልጠና ማእከል ግንባታ ፕሮጀክትም የ«ሀይቁ» መፍጠሪያ ስፍራ መሆኑ ነው::

የጠራው ሃይቅ ተፈጥሮ በጥምቀተኢህአዴግ ሚሊዮኖች የግስጋሴ፥ የዘመናዊና የቀልጣፋ አሰራር ተጋዳዮች ሊሆኑ ቢችሉ ነቃፊ ባልነበረ:: ነገር ግን ዛሬ ኢህአዴግ የያዘው ጉዞ አዲስ አይደለም:: ደርግ ራሱን የ«ልማት» ማእከል አድርጎ ሞክሮታል:: በውድና በግድ የኢሰፓ አባልነትንና ደጋፊነትን እያጎናፀፈ፥ በፖለቲካ ት/ቤት ውስጥ በገፍ አሰልጥኖ አቢዮታዊ ወኔን እየሞላ «አዲስ ስርአት» ሊገነባ «ለፍቷል»፤ አልፍቷል:: ያ ሁሉ «አቢዮታዊ ወኔ»ና «አዲስ ስርአት ግንባታ» ውስጡ የተቀውሞ፥ የቅጥፈትና የንቅዘት ሙላት ሆኖ አገርን ገድሏል:: ኢህአዴግም ዛሬ የተያያዘው የጥምቀት መንገድ ያንኑ ከመድገም የሚያድን አይደለም:: የመንግስት መስሪያቤቶችን የስራ ሂደት የማዘመኑ ትልቅ ፈተናም ይህ ነው::

የተጀመረው «ልማት» ውጤት የሆነው/የሚሆነው ያርሶአደርና የከተማ ሀብታምም ቢሆን ለኢህአዴግ ታማኝ ተጋዳይ ስለመሆኑ አንዳችም ዋስትና የለም:: የሰዎች የፖለቲካ አስተሳሰብ በኢኮኖሚ ጥቅም ብቻ አይወሰንም:: ከኢኮኖሚ ጥቅም ጋር ተዛምደውም ሆነ ተቃርነው አስተሳብን የሚወስኑ ሌሎች ፍላጎቶች አሉ:: የተማረውን ሙያተኛ በደሞዝና በጥቅም እየገዛሁ አንቶስቱሰዋለሁ የሚለው የኢህአዴግ እምነት ከሸፎ እንደቀረ ታይቷል:: ዛሬም እየታየ ነው:: ለመለስ ቡድን ሳይላዩን ሽር-ብትን እያሉና ወፍራም ደሞዝና ጥቅም እያነከቱ ከጆርባ ግን ጥርስ የሚነክሱ ቢሮክራቶችም ሞልተዋል::

አዲሱ የሀብታም አርሶ አደር የልማት ስትራቴጂ «ኪራይ ሰብሳቢነት»ን ዘግቶ በልማት መንገድ የመበልፀግን አማራጮች በሰፊው በመክፈት ትልቅ ስኬት አስገኝቷል እየተባለ የሚፎለለው ፉለላ ውስጡን ለቄስ ነው:: ቅድሚያ ነገር፥ ድሮም ሆነ ዛሬ ለብዙሃኑ አርሶአደር ከልማት መንገድ ውጪ ሌላ የእድገት አመራጭ የለም:: በመሬት ኪራይና በአራጣ መክበር ወይም በአርሶ አደሮች ላይ ተሹሞ በሙስና መጠቀም የጥቂቶች ነው:: ይህን የጥቂቹን «የኪራይ ስበሳቢነት» መንገድ አስቀርቻለሁ ከሆነ፥ የሰብል ዋጋን ከፍ አድርጎ ወደ ዩኒየኖችና ወደተሳካላቸው ገበሬዎች ገንዘብ ከከተማ መዛወር የ«ኪራይ ስበሳቢነት» ስልት ነው:: ለአርሶ አደሮች ካሳና መሬት እየሰጠ መንግስት ለኢንቨስተሮች መሬት አከራይ ስለሆነ የአርሶ አደሮች የርስበርስ የመሬት ኪራይ አይቀርም፤ አልቀረም:: ወደፊትም እየበለፀገ የሚሄደው አርሶ አደር የበለጠ ለመበልፀግ ተጨማሪ መሬት መፈለግ አንድ ምርጫው መሆኑ እውቅ ነው:: በሙስና መንበሽበሽ በዙሪያው ደርቶ እያለ፥ የሚያስጋ ተቃዋሚንና ደጋፊዎቹን (እስከ አርሶአደር ድረስ) ከህጎች/ከደንቦች በላይ በመሆንና በስውር ተንኮሎች ማጥቃት አጠቃላይ የስርአቱ ስልት ሆኖ እያለ፥ የኢህአዴግንና የመንግስትን መዋቅር እንዲመሩ እየተደረጉ ያሉት ሀብታም አርሶ አደሮችና ወደፊት ከተማውን የሚመሩት አዲስ ሀብታሞች ከንቅዘት ንፁህ የሚሆኑት በምን ተአምር ነው? መሰሪነትንና ስውር ስራን በማራባት ዋና አላሻቂ የሚሆነው ራሱ ኢህአዴግ ነው::

ለህወሃት ኢህአዴግ ሙሉ ገዢነት ጠንካራ መሳሪያ ከሆኑ ዘረፋቸው እዳው ገብስ ነው የሚል ስሌት ካለም አያዛልቅም:: ህወሐት/ ኢህአዴግን እንደ መንግስት ተቀብሎና አክብሮ ከዚያ

በታች ግለሰቦችንና ስንጥርጣሪ የመንግስት አካላትን መተቸት፥ መቃወም፥ በአቤቱታ ወይም በሰልፍ ማጋለጥና ማስቀየር የተፈቀደበት (ኢህአዴግ የሚፈልገው) «ዲሞክራሲ» ተቀባይነት የማግኘቱ ነገር ህልም ነው። የኢትዮጵያ ህዝቦች ግለሰቦች ላይ ከማተኮር ተሻግረው በድምጻቸው የሚቋቋምና የሚኖር መንግስትን ከጠየቁ ውለው አድረዋል። በተቃዋሚ ላይ ኢህአዴግ የሚያካሂደው መልከ ብዙና ጨካኝ ድቆሳ፥ በገዢው ቡድኑ ውስጥ ያለው ሀብት አካባችነትና የመለስ ህወሐታዊ ቡድን ዋና ተቆጣጣሪነት፥ ተያይዞም በሀገሪቱ ህዝቦች ብሄራዊ ጥቅምና ህልወና ላይ እየተሰሩ ያሉ መንግስታዊ ጥፋቶች ካጠቃላይ ቅዋሜ የማያላቅቁ ችግሮች ናቸው።

መልማት ለኢትዮጵያ ህዝብ መሰረታዊ ፍላጎት ነው። የሰላም እጦት እንዲወገድ ይሻል። የመለስ መንግስት እንደሚያስበውም የሚፈጥራቸው ትንንሽ ሀብታሞችም የብልፅግና ጉዟቸው በሰላም መረበሽ እንዳይደናቀፍባቸው አጥብቀው መፈለጋቸው እውነት ሊሆን ይችላል። የሰላም ፍላጎታቸው ግን ከተቃዋሚዎች ይበልጥ እራሱን የገዢውን ቡድን ጠልፎ የሚጥል ነው። ከተቃዋሚዎች ጋር መቀራረብና መደራደርን እምቢ ብሎ የኢትዮጵያ ህዝቦች የፖለቲካ መረጋገት እንዳያገኙ ችግር ሆኖ ያለው ራሱ ኢህአዴግ ነው። በሰላም ሊፈታው ያልቻለው የውስጥ ተቃውሞ ከጎረቤት ባለጋራነት ጋር ተሸራርቧል። የኢህአዴግ መንግስት በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ ላላው የሰላም እጦት ምክንያት ከሆኑት ኃይሎች አንዱ ሆኖ ለኢትዮጵያ የጎረቤት ጠላትነትን አበራክቷል። በሰሜን፥ በዘግናኙ ጦርነት ኢሳያስን ሳይቀጣ ተመልሶ፥ አሳፋሪ የድንበር ክርክር አድርጎና ቃል የገባበትን የፍርድቤት ውሳኔ የመቃበል ውሳኔ አጥፎ፥ ዛሬም ከኤርትራ መንግስት ጋር ፍጥጫ ውስጥ ነው። ከኤርትራ ጀርባ ሌሎች አበሮች አሉ። ከኤርትራና ካባሪዎቿ ጋር ያለው ትንንቅ ሶማሊያ ድረስ የተሻገረ ነው። የመለስን መንግስት ሶማሊያ ውስጥ ያስገባው የኢትዮጵያ ደህንነት ጉዳይ ሳይሆን ከሸአቢያ ጋር ያለው የመጣጣል ትንንቅና የአሜሪካንን ሽርክና በፀረሽብር በኩል አግኝቶ የስልጣን እድሜ የማርዘም ፍላጎት ነበር። ገብቶም ሽሪክ መንግስት አደራጃለሁ በሚል ሁለት አመት ሲዋጋ ቆይቶ ያስገኘው ውጤት የኢትዮጵያን የደሀ ጥሪት ማውደም፥ የሶማሊያን ቀውስ ማራዘምና[4] የሶማሊያን ባላጋራነት ማደስ -- **የኢትዮጵያን ደህንነት መጉዳት** ነው። የመለስ መንግስት ክስረትና ቂም አሸክሞን ሊወጣ ከወሰነም በኋላ የሚማር አልሆነም። አልሸባብ ሰልጣን የሚይዝ ከሆነ እንደገና ገብቼ ማውረዴ የማይቀር ነው እያለ ነው። ገና ከሶማሊያ ሳይወጣም፥ (የጎረቤት ጠንቀኛነትን ለማስወገድ በጎረቤት ፖለቲካ ውስጥ እጅን መስደድ ቆሞ፥ ከጎረቤትና ጎረቤትን ከተጠጉ ተቃዋሚዎች ጋር ድርድር ይደረግ ከማለት ይልቅ) ኤርትራ ካላረፈች እንውጋት የሚል ወፈፌ ምክር እየቀረበለት ነው። ኢህአዴግም ሰበብ እየጠበቀ መሆኑ ይታወቃል። ከሱዳን ጋር የተፈጠረው ወዳጅነትም መጽናቱ አጠራጣሪ እየመሰለ ነው። የኢህአዴግ መንግስት ከደቡብ ሱዳኑ ኤስ.ኤል.ኤም ጋር ሚስጥራዊ ወታደራዊ ቅርርብ በመፍጠር (እንደኬንያ መንግስት) እየታማ ነው። ተቃዋሚዎቹን «ፀረሰላም» የሚለው የመለስ መንግስት ሰላም አፍቃሪነት እስከዚህ ድረስ ነው።

---

[4] ለሶማሊያ ችግር መባባስ ተጠያቂነቱ የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግስት ብቻ አይደለም። የአፍሪካ ህብረት፥ተ.መ.ድ.ና ታላላቆቹ አገሮች ከተሻለ ጥረት ተቆጥበው በመቆየታቸው ተጠያቂዎች ናቸው።

**5)**ለገዢዎች የስልጣን ጥቅምና ለማይታረም ጅብደኝነታቸው ተብሎ ኢትዮጵያ በጠላትነት መከበብና ከጦርነት ወደጦርነት እየሄደች መከራ ማየት አይኖርባትም:: የኢትዮጵያ ህዝቦች ሁለገብ ልማት በህወሐት ኢህአዴግ ጥብቆ ፖለቲካና ጥብቆ ገዢነት ውስጥ ተሰንጎ ሲፈራገጥ የመኖር ወይም ዙሪያ ጥምጥም የመማሰን እዳ የለበትም:: የኢትዮጵያ የፖለተካ ቡድኖች ወደ እርቅ መምጣት፥ ሰፊ ትብብር መፍጠርና የዲሞክራሲ መብቶች ባግባቡ ህይወት ማግኘት ለኢትዮጵያ ሰላምና እድገት ወሳኝ በሮች ናቸው:: በነዚህ መሳሪያነት በባላገሩ፥ በከተሜውና በምህራኑ ነፃ ተነሳሽነት የተጥለቀለቀ እንቅስቃሴ በሁሉ መስክ መክፈት ይቻላል:: የኢትዮጵያ የሰለጠነ ባለሙያ ስደት አቅጣጫውን ለውጦ ከአገር ውስጥ እስከ ባህርማዶ በተያያዘ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ አፍቃሪዎች ርብርብ፥ የወደቀውን ትምህርት ማንሳትና የቴክኖሎጂና የዘመናዊ አሰራር መረጃዎችን ከያቅጣጫው እያሰባሰቡና እያቃኑ ለአገር ማዋል ይቻላል:: በአስደናቂ ፍጥነትና ወኔ የስራ ልሽቀትንና ሙስናን እየሰባበሩ በመንግስት የስራ አውታሮች ውስጥ ዘመናዊና ስነምግባራዊ አሰራርን (ታጥቦ ጭቃነት በሚቀርበት ሁኔታ) ማዳረስ ይቻላል:: ሴቶችን እየጎዱ ያሉት፥ የስራ ሸክም፥ ደፈራ፥ጠለፋ፥ ያለእድሜ ጋብቻና የመሳሰሉት ችግሮች የሚቃለሉት ሚንስቴር መስሪያቤት በመገተርና ዘወር ሲሉ እነበረበት ቦታ በሚመለስ የድብብቆሽ «ለውጥ» ሳይሆን ቀደም ብሎ እንደተባለው አገር በፈነቀለና ኑሮን በሚያነሳ፥ ወንዶችን ማደስ በሚችል (የተጠቃችውን ሳይሆን የአጥቂውን መንናቅ በሚያስከትል) አዲስ ግንባታ ነው:: የህግ የበላይነትና ዲሞክራሲም በማይቀለበስ ሁኔታ መሰረት ለመቆናጠጥ ምርጥ እድል የሚያገኙት በዚህ ማዕበላዊ ሂደት ነው:: የውስጥ ሰላምና ግስጋሴም ለአካባቢያዊ መጣጣም ብዙ ያግዛል:: **የኢትዮጵያ ህዝቦች እዚህ ምእራፍ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉበትን እድል ነው የተነፈጉት::**

የተነፈገውን እድል ለማስከፈት አንድም የረባ ትግል ከማድረግ ተቆጥቦ በህወሃት ኢህአዴግም በኩል ሆነ በተቃዋሚዎች በኩል ለህዝብ እየታገልኩ ነው ብሎ መኩራት አይቻልም:: «የጥላቻ ፖለቲካ አይጠቅመንም» እያሉ ባዶ ወሬ ማውራት ጆሮ አሰልችቷል:: የጥላቻ ፖለቲካን አውጋዥ ሁሉ ከጥላቻ ፖለቲካ በግድም በውድም ተወጥቶ የህዝብ ተነሳሽነት ነጻ የተለቀቀበት የልማትና የዲሞክራሲ ጉዞ ውስጥ እንዲገባ ለማስቻል እያደረገ ያለውን **ተጨባጭ ጥረት** ሊያሳየን ይገባል:: የኢህአዴግ ደጋፊ ወይም አባል ሆኖ « የቡድኖች እርቅ የስልጣን ፈላጊዎች ጥገኛ አመለካከት ነው»፥ «ዋነኛውና ተቀዳሚው ሰብአዊ መብት የኢኮኖሚ መብት ነው» እያሉ መወሸከት (የፖለቲካ ነፃነቶች ለኢኮኖሚ ልማት ያላቸውን የማረሻ ያህል መሳሪያነት መካድ) ለበር ጥበቃ የታሰራ ውሻ የሚሰራውን ስራ ከመስራት ወይም «እየፎገርኩ ልብላበት ተውኝ» ከማለት የተለየ አይደለም:: በተቃዋሚዎችም በኩል አላሰቀርብ ያለውና ሰላም እንዳይፈጠር ችግር የሆነው ኢህአዴግ ነው እያሉ ዛሬም ነገም ማውራት ተራ ስበበኛነት ነው::: በምንም መንገድ ፀረሰላም ብሎ መወንጀልና ማሰር በማይችልበት ታክቲክ፥ የውስጥና የውጪ ተቃዋሚዎች አፈና የቀለለበትን ሁኔታ በመፍጠር ግብ ላይ አንድ ድምጽ ሆነው እንዲደራደራቸው **አስጨንቀውት** ያውቃሉ? በዚህ አቅጣጫ መታገል (ለአጠቃላዩና ለ2002 ምርጫ) የሚኖረው የፖለቲካ ፋይዳ ለተቃዋሚዎች ገና አልተገለጣቸውም:: ላንዶንዶቹ የዚህ አይነት ጥያቄ ማንሳት ጊዜ ያለፈበትና ከ«ቁርጠኛ» የትጥቅ ትግላቸው ጋር የሚጋጭ ወይም

ከዚያ የሚያዘናጋ ነው። አንዳንዶቹም በኢትዮጵያ ላይ እቀባ እንዲደረግ ለፈረንጅ ደጅ መጥናት የተሻለ ውጤት የሚያመጣ ይመስላቸዋል። አንዳንዶቹ ፈረንጅ አገር ተቀምጠው ስለሁለገብ የትግል ስልት ያወራሉ። አባላትና ደጋፊ በመናጠቅ ስጋት የተጠማመዱ አሉ። በትብብር ጥያቄ ላይ የሚያንገራግሩም ይገጥሙናል። ፖለቲካንና ከስህተት መማርን እንደኮሶ ቢጋቱም እንኳ ለማይነቀንቃቸው ደግሞ ድርድር የሚባል ጥያቄ ማንሳት በጠላት እግር ስር ወድቆ የመለመን ክህደት ነው። የኢትዮጵያ ህዝቦች በጋራ የሚያብከነክኗቸውና አንድ ልብ የሚያደርጓቸው ህመሞች፥ ብሶቶችና ፍላጎቶች አሏቸው። ከነሱ የወጡት የፖለቲካ ቡድኖች ግን ቅዳጅና ጥብቆ አላማዎች ይዘው በተለያየ አቅጣጫ መገተርና የጎሪጥ መተያየት ሙያቸው ነው። የተማመነና አንድ ድምፅ ያለው ትግል አንዲት ጋት ድረስ እንኳ የማድረግ አስፈሪነት አልፈጠረባቸውም።

የመለስ መንግሰት የሚንቃቸውና በቀላሉ የሚከፋፍላቸው ለዚህ ነው። ተባብረው ይነሱብኛል የሚል ስጋት ሳይገባው የጠላውን ቡድን ሲቀለጥም ኖሯል። ዛሬም የኦነግ አባላት ናቸው ያላቸውን ከበረሃ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ከመልቀም አልፎ «ለአሸባሪው ኦነግ ከለላ ሰጪዎች» የሚል ስም በመስጠት በኦፌዴን እና ኦህኮ ላይ እያጉረጠረጠ ነው። ማጉረጥረጡ ለ2002 ምርጫ ችግር ፈጣሪ እንዳይኖርበት ከወዲሁ የማደንዘዝ አካል መሆኑም ግልጽ ነው። አውግዞ ተመልካች ከመሆን በስተቀር የዚህ አይነቱን ጥቃት የአጠቃላይ ቅዋሜ ማነሳሻ የማድረግና የአሸባሪነት ውንጀላን በድርድር ጥያቄ የማምከን ሙያ በተቃዋሚዎቹ ዘንድ ስለሌለ «አሸባሪና ጸረ-ሰላም እያልክ ማተራመስክን አቁም! የሰላምና የድርድር ጥያቄው የኛም ጥያቄ ነውና ተቀበል!» የሚል የህዝብ መነሳሳት አያሰጋውም። እናም «አሸባሪዎች»ን ሲያስር አሸባሪ አትሰር አይባል ነገር ሰለሚሆንበት ህዝብ ዝም ብሎ ከማየት ሌላ ምርጫ የለውም። ኦፌዴንና አህኮም «ከለላ አይደለንም» እያሉ ከመወራጨት በላይ የሚያመጡት ነገር አይኖራቸውም። ወደፊት ውንጀላውን አጠናክሮ ለአዲስ አበባ እንኳ የሚሆን ሥር ሲያሳጣቸው እናይም ይሆናል።

ተቃዋሚዎች እንደማያደርጉት በማመኑ መለስ ዜናዊ በፓርላማ ፊት ኦነግ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ህገመንግስቱን ከተቀበሉ ለመደራደር ዝግጁ ነን ብሎ ለመናገር ደፍሯል። ልብ በሉ! ቡድኔ ምርጫ ቦርድን፥ የጸጥታውን ክፍልና ሌላ ሌላውን እንደንብረቱ መጠቀሙን ተቀበሉ አላለም፤ ህገመንግስቱን ተቀበሉ ነው። ከመለስ አምባገነንነት ጋር ህገመንግስቱም ካልፈረሰ ሽረት የለም ብለው የሚያስቡ ካሉ ከነዚህ ጋር ጉዳይ የለንም። ህገመንግስቱ የመለሳቸው ጥያቄዎች እንዳሉ ሁሉ መታረም ያለባቸውም ነገሮች አሉ፥ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ህገመንግስቱ ሊያሰራን ይችላል፥ ችግር የሆነብን የገዢው ቡድንና የጭፍሮቹ ጥሰት ነው የሚሉት ግን ህገመንግስቱን እንድታከብርና ይህ ይህ አሰራርህ መቃኛ እንዲደረግለት እንፈልጋለን በሚል ጥያቄ ለምንድን ነው የማይመጡበት? ያንዳንዶቹ መልስ «አይፈጸምም፥ ኢህአዴግ አይታረምም» የሚል እንደሚሆን ይገመታል። ባይፈጸምስ? እጅ እግር አጣጥፋችሁ መልስ ጠብቁ ወይም የሀይል ትግል ከድርድር የፈጠነ ውጤት የሚያመጣ ሲሆን ዝለሉት አልተባለም። አዲስ ሁኔታ እስከሌለ ድረስ በዚህ መንገድ የፖለቲካ ዘመቻ መክፈት ገዢውን ቡድን የበለጠ በመክሰር ወይም ተገዶ አፈናን በማላላት አጣብቂኝ ውስጥ አያስገባውም? እነአሜሪካንን አግዙን ለማለትስ የበለጠ ጉልበት አይሰጥም? ጥያቄው ይህ ነው። የተጋለጠው የገዢው ተፈጥሮ ተመልሶ እንዳይሸፈንና

ክስረቱ እንዲጨምር የመስራትን እቅድ በወረቀት ላይ ያሰፈሩትስ እቅዳቸው እዚህ ድረስ የረዘመ ትልም የለውም? ወይስ እንዲህ ያለ የድርድር ጨዋታ እርምን መብላት ሆኖባቸዋል?

ራስን እንኳ የማያድን ትንንሽ የፖለቲካ ጥብቆነት እስከቀጠለ ድረስ፥ ትግሉ በእሾክ አጥር ውስጥ እንደተሰነቀረች ወፍ ከመንደፋደፍ አይወጣም። የአገሪቱና የህዝቦቿ የወደፊት ጉዞም በህወሐት/ኢህአዴግ የሚወሰን መሆኑ ይቀጥላል።